# መጽሐተ ፡ ጥበብ ።
# ዘአለቃ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ።

በትምህርትና ፡ በጥበበ ፡ ሚኒስትር ፡ ፈቃድ ፡
ሺ፱፻፵፩ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተጻፈ፡

በልዑል ራስ መኰንን ማተሚያ ቤት ፲፱፻፵፯ ዓ ም ታተመ።
አዲስ አበባ ። ቁ ፩

ማውጫ ።

| ግድፈት | መስመር ። | እርማት ። | ገጽ |
| --- | --- | --- | --- |
| የሠራውን ። | ፳ | የሥራውን ። | ፲፬ |
| ከጐድጓዳ ። | ፲ | ከጐደጓዳ ። | ፳፫ |
| መሥሯ ። | ፲፰ | መሣሪያ ። | ፳፯ |
| መሣሪ ። | ፳ | መሣሪያ ። | ፳፱ |
| መስልኩ ። | ፯ | መሰልኩ ። | ፴ |
| አማሪኛ ። | ፩ | አማርኛ ። | ፴፩ |
| ሲጸራበት ። | ፯ | ሲጸራት ። | ፴፫ |
| የትዘራውንም ። | ፳፪ | የተዘራውም ። | ፴፫ |
| አንደ ፣ ቀደመው ። | ፲፯ | እንደ ፣ ቀደመው ። | ፴፱ |
| ያናት ። | ፲፯ | የናት ። | ፵፩ |
| ጥቅርሽ ። | ፱ | ጥቀርሽ ። | ፵፪ |
| በጥ ። | ፲፯ | በጠጥ ። | ፶ |
| ያየሚነቃ ። | ፪ | የሚያነቃ ። | ፶፯ |
| ይጠድቀና ። | ፫ | ይጠድቅና ። | ፶፯ |
| ቢዶ ። | ፲፯ | ቤዶ ። | ፷፪ |
| ነመን ። | ፰ | ኅመን ። | ፷፱ |
| ጊዶ ። | ፲፰ | ጉዶ ። | ፸፩ |
| ባሕር ፰ ። | ፳፩ | ባሕር ፣ ክፍሎ ። | ፸፩ |
| ድቢጥ ። | ፳ | ድምቢጥ ። | ፸፬ |
| ተስበ ። | ፱ | ተሳበ ። | ፸፮ |
| የለወም ። | ፫ | የለውም ። | ፹፬ |
| እንዳመጣ ። | ፲፩ | እንዲመጣ ። | ፹፭ |

## ማውጫ ።

| ግድፈት | መስመር | እርም | ገጽ |
|---|---|---|---|
| በበላችሁ ፡ ጊዜ። | ፰ | በበላችሁ ፡ ጊዜ ፡ | ፪፻፩ |
| ነንዳሳታት ። | ፲፮ | እንደሳታት ፡ | ፪፻፩ |
| ሥጋን፡ተዋሕዶ። | ፲፯ | ሥጋን ፡ ተዋሐደ። | ፪፻፫ |
| ተ)ፈጠረ። | ፩ | )ተፈጠረ ፡ | ፪፻፲፫ |
| በመንገሀ። | ፲፰ | በመንገድህ ፡ | ፪፻፲፫ |
| ጐዳይ ። | ፲፫ | ጉዳይ ፡ | ፪፻፲፰ |
| አቀርበ ። | ፪ | አቅርቦ ፡ | ፪፻፳፫ |
| አወጣቸው ። | ፫ | አውጣቸው ፡ | ፪፻፵፯ |
| የኃጢአተኛ ። | ፳፫ | የኃጢአተኛን | ፪፻፵፱ |
| የምትስቀይበት ። | ፪ | የምትሰቅዩበት ፡ | ፪፻፵፩ |
| ድንቀ ። | ፲፩ | ቀንድ ፡ | ፪፻፵፱ |
| ያያዘ ። | ፲፪ | የያዘ ፡ | ፪፻፶ |

1714

# መጽሐተ ፡ ጥበብ ።
## ዘአለቃ ፡ አፈ ፡ ወርቅ ።

በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ ሚኒስትር ፡ ፈቃድ ፡
ሺ፱፻፳፭ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ ተጻፈ ፡

በልዑል ራስ መኰንን ማተሚያ ቤት ፲፱፻፳፮ ዓ ም ታተመ ።
አዲስ አበባ ። ቁ ፩

የኢትዮጵያ፡የማነጋገሪያ፡ምርምራ
የብሔ... መጻሕፍ... ቤት ።
ኢንስቲቱት ፤

የዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ ቤተ መጻሕፍት
አዲስ ፡ አበባ
Addis Ababa
University College Library

# ማ ስ ረ ጃ ።

በትምህርትና ፡ በጥበብ ፡ ሚኒስትር ፡ በክቡር ፡ ብላቴን፡ ጌታ ፡ ማህሴ ፡ ፀዳሉ ፡ ፈቃድ ፡ ይህን ፡ መጽሐፍ ፡ ለመጻፍ፡ ያሰብኩበት ፡ ምክንያት ፡ ስለ ፡ ሁለት ፡ ነገር ፡ ነው ።

አንደኛ፤ ቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ የኢትዮጵያ ፡ ንጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ሐሳባቸውና ፡ ቸርነታቸው ፡ ሁሉ ፡ አገራቸውን ፡ ኢትዮጵያን ፡ ከፍ ፡ ከፍ ፡ እያደረጉ ፡ ወደ ፡ ታላቅ ደረጃ፡ለማድረስና ፡ ወጣቶች ፡ ልጆችዋ ፡ ሁሉ፡በዕውቀትና፡ በሥልጣኔ ፡ ከጎረቤቶቻቸው ፡ ጋራ ፡ እንዲተካከሉ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ በአዲስ ፡ አበባና ፡ በያውራጃውም ፡ ሁሉ ፡ በፈረንሣዊና ፡ በእንግሊዝ ፡ ቋንቋ ፡ የሚማሩበት ፡ ዓሥራ ፡ ሦስት ፡ ያህል ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ አቁመው ፡ ብዙ ፡ ወጣቶች ፡ ይፈልቁበታል። የንባብና ፡ የዜማ፤ የቅኔና ፡ የሊቃውንት ፡ ጉባዔ ፡ ተማሪ ፡ ቤት ፡ ግን ፡ በኢትዮጵያ፡በያውራጃው ፡ የቆሙት ፡ እጅግ ፡ ብዙ ፡ ናቸውና ፡ አሁን ፡ እዚህ ፡ ዘርዝረን፡ለመጻፍ፡ አላስፈለገንም። ነገር ፡ ግን ፡ ምንም፡የትምህርት ፡ መሠረት ፡ ቋንቋ ፡ ስለ ፡ ሆነ ፡ የሐዋርያት ፡ ሥራ፡ ምዕራፍ ፡ ፪፡ቁጥር ፡ ፬ ፡ እስከ ፡ ፲፫። ቆሮንቶስ ፡ ፩ ፡ ምዕራፍ ፡ ፲፬ ፡ ቁጥር ፡ ፱።

ሀገር ፡ ለማቅናትና ፡ ለመንግሥት ፡ እርዳታ ፡ የሚሆን፡ ብዙ ፡ ገንዘብ ፡ ለማግኘት ፡ ያለ ፡ እጅ ፡ ሥራ ፡ አይቻልም። ዋና ፡ የእጅ ፡ ሥራ ፡ መሠረትም ፡ ማለት፡ ከመሬት፡ የሚገኝ

ግምባር ፡ ቀድም ፡ ሁኚ ፡ ሀገር ፡ እያቀናሁ ።
ያ ፡ ክርፋታም ፡ ፋቂ ፡ ሲባባሉ ፡ ሰማሁ ።
ጓደኛን ፡ መናቅ ፡ ሞያ ፡ መስሏቸው ።
ሕይወታቸውን ፡ ጠሉ ፡ በሞኝነታቸው ።
እነሱ ፡ ቢንቁኝ ፡ እኔ ፡ ላክብራቸው ።
ከጄም ፡ እንዳይወጡ ፡ ጥገኛዬ ፡ ናቸው ።
አሁን ፡ ያገኙኛል ፡ ማታ ፡ ከጉድጓዳቸው ።

ተፈጸመ የፋቂ ሥራ ለእግዚአብሔር ክብር ይግባው

ምዕራፍ ፡ ፲፮ ።

የሸክላን ፡ ሥራ ፡ መጀመሪያ፡ ከራሱ ፡ አንቅቶ ፡ ከልቡ ፡ ናው ፡ ሐዲስ ፡ ጥበብ ፡ አውጥቶ ፡ ፈልስፎ ፡ አፈሩንና ፡ ድንጋዩን ፡ በየዓይነቱ ፡ እያደቀቀ፡ አልሞ ፡ በመዘውር ፡ እያመላለሰ ፡ ከበረበሩ ፡ መሬት ፡ መዳብና ፡ ናስ ፡ ከአበልሴው ፡ ከገሀው ፡ መሬት ፡ ቆርቆሮ፡ እይር፡(ቅልቅል)እንደ፡ አይራ ፡ እንደ ፡ እንጠጠ ፡ ካ ለው ፡ መሬት ፡ ብረት ፤ እንደ ፤ ቋራ ፤ እንደ ፤ ወለጋ ፤ ካለው ፡ መሬት ፡ ወርቁን ፡ ለብቻው ፡ ለይቶ ፡ አስቀርቶ ፡ አፈሩን ፡ በወሀ ፡ ለውሶ፡በጣም ፡ ሲቦካ ፡ በእግሩ ፡ ረግጦ ፡ በእጁ ፡ ጭቃውን ፡ አለዝቦ ፡ ለሰው ፡ እንደሚያስፈልገው ፡ አድርጎ ፡ የሠራው ፡ የረዓይት ፡ ወገን ፡ የሚሆን ፡ አዛዝኤል ፡ ይባላል ።

ክፍል፡ ፩ ።

እኒህ ፡ ረዓይት ፡ የሚባሉ ፡ ፍጥረቶች ፡ ታሪካቸው ፡ ከዚህ ቀጽሎ ፡ እንደ ፡ ተጻፈው ፡ ነው። ቃየል ፡ ወንድሙን ፡ አቤ



ልን ፡ በእኅቱ ፡ ቀንቶ ፡ ከገደለው ፡ ጀምሮ ፡ በአዳምና ፡ በሔዋን ፡ ኃዘን ፡ እጅግ ፡ ጸንቶባቸው ፡ ነበርና ፡ በባልና ፡ በሚስት ፡ ልማድ ፡ ሳይገናኙ ፡ ብዙ ፡ ዘመን ፡ ከኖሩ ፡ በኋላ ፡ መልአክ ፡ መጥቶ ፡ አዳምን ፡ ልጅህ ፡ በግፍ ፡ ስለሞተ ፡ በነፍስ ፡ ተጠቅሟልና ፡ አትዘን ፡ ብሎት ፡ ሚስቱን ፡ ሔዋንን ፡ በግብር ፡ ሳላወቃት ፡ አረገዘችለትና ፡ ሴት ፡ የሚባል ፡ ልጅ ወለደችለት ፡ ሴት ፡ ምትክ ፡ ማለት ፡ ነው ፡ አቤል ፡ ከሞተ በኋላ ፡ ስለወለደው ፡ የልጁን ፡ የአቤልን ፡ ምትክ ፡ ወለድኩ ስለማለት ፡ ስሙን ፡ ሴት ፡ ብሎታል። ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፬ ፡ ቍ ፳፭ ፡ ሴትም ፡ ሄኖስ ፡ የሚባል ፡ ልጅ ፡ ወለደ ፤ ሴትም ፡ መቶ ከምስት ፡ ዓመት ፡ ኑሮ ፡ ሄኖስን ፡ ወለደ። ዘፍጥ ም ፡ ፭ ቍ ፮ ። ሄኖስም ፡ ዘጠና ፡ ዓመት ፡ ኑሮ ፡ ቃይናንን ፡ ወለደ ፡ ቃይናንን፡ከወለደ ፡ በኋላ፡ ስምንት፡ መቶ ካሥራ ፡ አምስት ፡ ዓመት ፡ ተቀመጠ ፡ ወንዶችና ፡ ሴቶች ፡ ልጆች ፡ ወለደ ፡ በዘጠኝ ፡ መቶ ፡ አምስት ፤ ዓመቱ ፡ ሞተ ፤ ዘፍጥ ፡ ም ፡ ፭ ፡ ቍ ፤ ፲ ፡ ፲፩ ። የሄኖስ ፡ ልጆችና፡ የሴት ፡ ልጆች ፡ ከሴቶች ፡ ርቀን ፡ ንጽሕና ፡ ጠብቀን ፡ እንደ፡ መላእክት ፡ እግዚአብሔርን ፡ እያመሰገን ፡ እንኖራለን ፡ ብለው ፡ ብፅዓት ፡ ገብተው፡ (ስለት ተስለው)፡ በገነት ፡ አጠገብ ፡ ደብር ፡ ቅዱስ ፡ በዓተ ፡ መዘግብት ፡ በሚባል ፡ቦታ ፡ ሲኖሩ ፡ ከነዚያ ፡ አንዱ ፡ ሀገር ፡ ለማየት ፡ ወጥቶ ፡ ሳለ ፡ የቃየል ፡ ልጆች ፡ ከሚኖሩበት ፡ ምድረ ፋዩድ ፡ ከሚባል ፡ ሀገር ፡ ደረሰ።ገድለ ፡ አዳም ፡ መቅድመ ፡ ወንጌል። ለቃየል ፡ መልክ ፡ መልካሞች ፡ ብዙ ፡ ሴቶች ፡ ል

ማይታወቅ ፡ ረቂቅ፡ መንፈስ ፡ ቅንአት ፡ የተመሠረተ ፡ ምክር ይመስለኛል ።

መወድስ ፡ ስለ ፡ ቅንአት ፡ ልዩነት ፡ ።

መኑ ፡ ዘርእየ ፡ በኅብረ ፡ አሐዱ ።

አካለ ፡ ቅንዓት ፡ ረቂቅ ፡ መልክዐ ፡ ብእሲ ፡ ውብእሲት

እስመ ፡ ለለዕለት ፡ይትቄለጥ ፡ ኅብረ ፡ መልክዑ ፡ሐሰት

ወነገረ ፡ ዝ ፡ ያጠይቀነ ።

ተመሰለ ፡ በመልክዐ ፡ ንስር ፡ መልክዑ ፡ ለሞት።

ወእንዘ ፡ ልብሰ ፡ ውስጥ ፡ ሐራውያ።

ልብሰ ፡ ካህነ ፡ ዕርዕ ፡ ይመስል ፡ አልባሰ ፡ አባግዕ ፡ ወ አልሕምት።

አስተርአየኒ ፡ ንጽሐ ፡ ሶስና ፡ መልክዐ ፡ መላእክት ቀደምት ።

በኅብረ ፡ መካሕ፡ ብእሴ ፡ ኃይል ፡ ለዐቀብተ ፡ ፍትወት ረበናት ።

ወለትንሣኤ፡ወልድ ፡ ፀሐይ ፡ ኩናኔ ፡ ሙስና ፡ መዓልት

ቅንዓተ ፡ አይሁድ ፡ አስተማሰሎ ፡ በጽልመተ ፡ ዓይን ኅብረ ፡ ሰረቅት ።

አለቃ ፡ አፈወርቅ ፡ ዘነቀምት ፡ ወልዱ ፡ ለቅዱስ ፡ ማ ርቆስ ፡ ኦርቶዶክሣዊ ፡ በቀዳማዊ ፡ አፄ ፡ ኃይለ ፡ ሥላሴ ፡ን ጉሠ ፡ ነገሥት ፡ ዘኢትዮጵያ ፡ መንግሥት ፡ በክቡር ፡ ብላ ቴን ፡ ጌታ ፡ ሣህሌ ፡ ፀዳሉ ፡ የትምህርትና ፡ ጥበብ፡ ሚኒስት ርነት ፡ በብፁዕ ፡ አቡነ ፡ ቄርሎስ ፡ ዘመንግሥተ ፡ ኢትዮ



ጵያ ፡ ሊቀ ፡ ጳጳስነት ፡ በ፲፱፻፳፯ ፡ ዓመተ ፡ ምሕረት ፡ በል ዑል ፡ ራስ ፡ መኰንን ፡ መታሰቢያ ፡ ከሣቴ ፡ ብርሃን ፡ ማተ ሚያ ፡ ቤት ፡ ታተመ ።

ያናጢ ፡ ሥራ ፡ተፈጸመ ፡ ለእግዚአብሔር ፡ ክብር ፡ይግባው

## ማውጫ ።

| | ምዕራፍ | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| መምህር | ፩ | » | ፳፫ |
| ስለ ፡ እርሻ ። | ምዕ ፡ ፪ | » | ፳፭ |
| ስለ ፡ ገበሬ ፡ ዕቃ | » | ፩ | ፳፮ |
| ስለ ፡ መሬት ፡ መልክ | » | ፪ | ፴ |
| ስለ ፡ መሬት ፡ ቅመም | » | ፫ | ፴፪ |
| ስለ ፡ መሬት ፡ ጠባይዕ ። | » | ፬ | ፴፪ |
| ስለ ፡ መሬት ፡ አስተራረስ ። | » | ፭ | ፴፮ |
| ስለ ፡ ዘር ፡ አመራረጥ ። | » | ፮ | ፵፪ |
| ስለ ፡ ጉበስ ፡ ዓይነት ። | » | ፯ | ፵፬ |
| ስለ ፡ አገዳ ፡ እህል ። | » | ፰ | ፵፮ |
| ስለ ፡ ሽምብራ ። | » | ፱ | ፵፰ |
| ስለ ፡ ቅባት ፡ እህል ። | » | » | » |
| ስለ ፡ ወጥ ፡ እህል ። | » | » | » |
| ስለ ፡ ቅመም ፡ እህል ። | » | ፲ | ፵፱ |
| ስለ ፡ ጥጥ ። | » | ፲፩ | ፶ |
| ስለ ፡ ምሳሌ ፡ ዘር ። | » | ፲፪ | ፶፩ |
| ስለ ፡ ሥራሥር ፡ ምግብ ። | ምዕ ፡ ፫ | » | ፶፫ |
| ስለ ፡ ቆሎ ፡ (በዶ) ። | » | ፩ | ፶፬ |
| ስለ ፡ እንሰት ። | » | ፪ | ፶፬ |
| ስለ ፡ ጎደሬ ፡ (በዶና) ። | » | ፫ | ፶፮ |
| ስለ ፡ ነጭ ፡ ሽንኩርት ። | » | ፬ | ፶፯ |
| ስለ ፡ ተክል ፡ ዓይነት ። | ምዕ ፬ | » | ፶፯ |
| ስለ ፡ ትርንጎ ። | » | ፩ | ፶፯ |
| ስለ ፡ በኡረ ፡ ሎሚ ። | » | ፪ | ፶፯ |

## ማውጫ።


| | ምዕራፍ | ክፍል | ገጽ |
|---|---|---|---|
| ስለ ፡ ዋልታ ። | » | ፩ | ፩፻፳፬ |
| ስለ ፡ ዕንጨት ፡ ምሳሌ ። | » | ፪ | ፩፻፴ |
| ስለ ፡ ዮናስ ፡ ስብከት ። | » | ፫ | ፩፻፴፩ |
| ስለ፡ ዕንጨትና፡ ሰው፡ ተፈጥሮ ። | » | ፬ | ፩፻፴፮ |
| ስለ፡ ጠማማና፡የቀና ፡ ዕንጨትምሳሌ | » | ፭ | ፩፻፴፯ |
| ስለ ፡ ሠራተኛ ፡ ጥቅም ። | » | ፮ | ፩፻፴፱ |
| ስለ ፡ ነቀፋ ፡ አለመጕዳት ። | » | ፯ | ፩፻፵ |